
# ሐዋርያ ጋዜጣ ከኢንጅ. ሃይሉ ሻዎል ጋር ቆይታ

*"...ብዙ ጊዜ ስህተት አድርገናል። አለም አቀፍ ድርጅቶች እኛን ይደግፉሉ፥ ለዴሞክራሲ ቆመዋል የሚባል ብዙውሬ አለ።ይሄን በአሁኑ የትግል ሂደት ትክክል እንዳልሆነ ተረድተናል። ስለዚህእኛ በራሳችን ሰዎች፥ በኢትዮጵያናውጭ ባሉ ወገኖች መመካት እንጅ ሌሎች አለም አቀፍ ድርጅቶች መጥተው ይረዱናል ብሎ መገምነቱ ከንቱ ነው።"*

**ክቡር ኢንጅነር ሃይሉ ሻወል፥ የቅንጅት ለአንድነትና ዴሞክራሲ ፓርቲ ፕረዚደንት**



*የሐዋርያ እትም እየዘገየባችሁ ያሰባችሁ እንዳላችሁ ይረዳናል። መዋል ማደር ሲበዛ፥ ስጋቱ ከሐዋርያ ወዳጆችና አንባቢዎች ብቻ ሳይሆን፥ ምስጋና ይግባቸውና ጥቂት አጉል ባተሌዎችና ለራስ እያውቄዎች የጎዳን መስሏቸው የሐዋርያን ባህርይና ይዘት ፖለቲካዊ ቅኝት ሰጥተው ለተለያዩ ተቋማት ስላስተዋወቁን፥ ተቋማቱ በተቃራኒው ጋዜጣችን*

*እንዳልባሌ ህትመት ሳይሆን በቁም ነገረኛነት ቆጥረዋት ስትዘገይ ይጠይቃሉ፥ ተስፋ እንዳንቆርጥ ያበረታታሉ፥ ለአዘጋጆችም የሚገባውን ክብር ይሰጣሉ። በበኩላችን ተስፋ መቁረጥ ከጅሎን አያውቅም፣ አቅምና ጊዜ አልገጣጠም እያሉ ሚዛ ቸውን እየለካን እንጅ።*

*የህትመት ጊዜዋን ጠብቆ ሐዋርያን የማስቀጠሉ ፍላጎትና እምነት እንዳለ ሆኖ፥ ለዚህኛው ወር ዝግጅታችን ብዙዎቻችን በፖለቲካ ስብእናቸው የምናከብራቸውን መሪ የክብር እንግዳችን አድርገን ይዘን ቀርበናል። እንግዳችን ክቡር ኢንጅነር ሃይይሉ ሻዎል፥ የቅንጅት ለአንድነትና ዴሞክራሲ ፓርቲ ፕረዚዳንት ናቸው። ለኢትዮጵያና ሕዝቧ የሚያስቡትን፥ የእስካሁኑን ተመክሯቸውንና የወደፊቱን የኢትዮጵያ እጣ ፋንታ ጠይቀናቸው አጫውተውናል። ከብዙ በጥቂቱ ከዘገብነው እነሆ፣ መልካም ቆይታ።*

**<u>ሐዋሪያ፦</u> ብዙ ወገኖቻችንን ሲያሳስቡ ከቆዩ ጉዳዮች መካከል አንዱ ከተቃዋሚ ድርችቶች መካከል የአንዱ የቅንጅት መሪ የሆኑት የእርስዎ የኢንጂነር ኃይሉ ሻዉል ጤንነት ጉዳይ ነበር አሁን ጤንነትዎ በምን ደረጃ ላይ እንዳለ ቢገልጹል?**

<u>ኢንጅ. ሃይሉ፦</u> የጤንነቴ ጉዳይ በጣም ጥሩ መጥቷል አሁን። በፊት የነበረው ችግር ሁሉ ተወግዷል። ሃኪሙም በቃ ድነሃል ሂድ፣ አገርህ ከመመለስህ በፊት ግን አንዴ ምርመራ አድርገህ ብትመለስ ጥሩ ነው ብሏል። ሰው ሃኪምቤት ሲተኛ ሰውነቱ ስለሚዳከም ያንን ጡንቻ በእንቅስቃሴ ማፍታትት ወይም ማጠንከር ብቻ ነው የሚያስፈልገው።

<u>ሐዋርያ፦</u> የግንቦት 1997 ብሄራዊ ምርጫ ድክመቱና ጥንካሬው ምን ነበር ይላሉ? ከዚያ ሕዝባዊ ማዕበል የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሃይሎችና ሕዝቡ የሚማሩት ተመክሮ ምንይመስሎዎታል?

<u>ኢንጅ. ሃይሉ፦</u> ይሄ ምርጫ መቸም የኢትዮጵያን ሁኔታ በእኔ አስተሳሰብ ማለቴ ነው የሕዝብን አስተሳሰብ የለወጠ፣ የገዥውን ፓርቲ ያስደነገጠና የዓለምን ትኩረትም የሳበ ነው። አንዳንድ ሰዎች ይህንን ምርጫ መግባት አልነበረብንም ይላሉ፣ እነሱም ምክንያት አላቸው። ችግር ይፈጠር እንደነበር አውቀናል፣ ነገር ግን ምርጫ አንገባም ብንል ይህ መውንግስት ዴሞክራት ነው እየተባለ ለዘላለም እንደሚመሣደቁብን ስለታየ ነው። ብዙዎቹን የእኛን ሕዝብ ገጠል ያህለርውን እንዲመርጥ ከእንግዲህ ወዲህ መንግሥት ለመለወጥ ከፈለግህ መሥእሪያ አያስፈልግህም ብለን ሦስት ዓመት በላይ ሠርተናል። ያንን ሳናሟላ፣ ያንን ጥያቄ ወደ ሁውላ ብንል እንዲህ ብላችሁን ነበር ይህልላ። ያን ጊዜ ከዚያ ምርጫ ለመውጣት አንችልም። የማንችልበትንም ምክንያት ለሕዝብ ነግረናል። ከሕዝብ ጋር እንጣላለን፣ ሁለተኛም ደግሞ፥ ይሄ መንግሥት ዴሞክራሲ እያለ ሁልጊዜ ሲመሣደቅ የነበረውን ሳናጋልጥ እንቀራለን። አሁም ቢሆን የተደረገው የትግል ሁኔታውን አፋፋምን እንጅ አላዳፈነውም። በእኔ አስተያየት አንድ ምእራፍ ወደ ፊት ሄደናል ማለት ነው። ሦስተኛ፥ ያን ጊዜ የውጭ መንግስታት " አይ ይህ መንግሥት ዴሞክራት ነው እናንተ ስም ብላችሁ ነው የምትጮሁት" እያሉ በዲያስፖራ ያላችሁትን ሁሉ ሲያንኳስሱ ነበር። ነገር ግ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያንን አይነት ምድር አንቀጥቅጥ ሰልፍ ይዞ ሲወጣ ከዚያ በሁዋላ ደግሞ ያንን ዓይነት ሥርዓት ይዞ በምርጫው እስከመጨረሻው ወሳኝነቱን ሲያሳይ ዳግም የሚመሣደቁበትን አፋቸውን አዘግቶልናል። ስለዚህ በነዚህ ሦስት ጉዳዮች ወደ ምርጫ መግባታችን ትክክል ነው። ምርጫ ስንገባ ለወደፊት ምን አዘጋጅተን ነው? በቀላሉ የሚለወጥ ነገር አይደለም፣ ባለፈው ምንድን ነው የሆነው፥ ምርጫ ሲደረግ ቦርዱ ይለወጥ፥ ይሄ ይሄ ይዘጋጅ ብለን ሞክረን ምንም አይነት ለውጥ ወይም ንቅናቄ ባለመኖሩ ከውስጥም ከውጭም በወሬ እንጅ እውነተኛ ድጋፍ ባለመኖሩ የግዴታ በዚያ ምርጫ መግባት ተገደናል። አሁን ግን ብዙ ጉዳዮች መሟላት አለባቸው። መሟላት ያለባቸው በጣም ከባድ ሁኔታወች አሉ። ከዚህ በፊትም ብዙዎቹን ጥያቄዎቻችን ተጽፈው ወጠው አይታችሁዋቸዋል። እኛ ከእንግዲህ ይህን ሕዝብ ምርጫ ግባ ብለን የምናጋልጥበት መንገድ አይኖርም። ስለዚህ ለሌሎቹም የምንመክረው ይህን ነው። እንዲሁ በተንቀዥቀዠ (በተቻኮለ) ሁኔታ ሊገቡ እንዳሉ እናውቃለን። እነዚህ ደግሞ በጣም ትናንሽ ፓርቲዎች ናቸው እንጅ የሕዝብ ድጋፍ ኖሯቸው ሕዝብ አስከትለው የሚሄዱ አይደሉም። ስለዚህ ለምን ምርጫ እንደሚገቡ ብንመለከት የፓርላማ መቀመጫ ወንበር ወይም የወረዳ ገዥነት ቦታ ለማግኘት ካልሆነ በስተቀር አንድም ጋት ያክል ወደፊት የሚያስኬድ ለውጥ አይገኝም። ሌሎቹም ፓርቲዎች እንደዚሁ ጥንቃቄ አድርገን እርስ በርሳችን ተነጋግረን፥ ተማምነን፥ አንድ ላይ ቆመን እምቢታም፥ እሽታም ቢኖር ጥሩ ነው። አሁን ባለው ሁኔታ ግን የሚቻል አይመስለኝም። ጥቃቅን ፓርቲዎች እዚያ ያሉት እንደዚሁ ለሕዝብ ለማስመሰል እንጅ፥ ለሕዝብ የማይሠሩ ስለሆነ፥ እኛን ሳያካትት ሌሎቹ መግባታቸው አይቀርም።

<u>ሐዋርያ፦</u> ቅንጅት አንዱ የኤ.ኤፍ.ዲ (ሀህሃ) መሥራችና አባል ሆኖ በመቀጠሉ ብዙ ወገኖች በመገረም ይወያዩበታል። ጉዳዩ ትብብሩ በተፈጠረበት ወቅት ብዙ ጥያቄዎችን ጭሮ አያሌ ኢትዮጵያውያን በውይይት እንደተፋጩበት ይታወሳል። ከዚያ በሁዋላም ይህ የትብብር ጅምር በግልጽ እንቅስቃሴ ሲያደርግ አይስተዋልም ብቻ ሳይሆን መሥራቾቹ በተለይቅንጅት አንድም ነገር ስለዚህ እንቅስቃሴ ለሕዝብ በግልጽና በይፋ የገለጸው ነገር የለም። በዚህ ላይ ለሕዝብ ግልጽ ማድረጉ ምናልባት ወቅቱ ነው ካሉ ቢያብራሩልን?

ኢንጅ. ሃይሉ፡- ኤ ኤፍ ዲ የተመሠረተው ከኢትዮጵያ ውጭ ነው፡፡ ከኢትዮጵያ ውጭ በነበሩ፥ በዚያን ወቅት ቅንጅት ነን ብለው በሚንቀሳቀሱ ሰወች አመካኝነት ነው፡፡ ግን ቅንጅት የተባለው ሁለት ቦታ ተከፋፍለዋል እነዚያ ሰዎች፡፡ እኛ ስንወጣ እኛን ከሚደግፉ ሰዎች ምንም መረጃ አላገኘነም፡፡ ምንም አልሠሩም፤ የሚሠሩትም ነገር አልታየኝም፡፡ በአጠቃላይ ግን የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ወገኖች በምንም መንገድ የኢትዮጵያን አንድነት ስከጠበቁ ድረስ በፈለጉት መንገድ ተደራጅተው አንድ ላይ ሆነው በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠው የኢትዮጵያን ጉዳይ እንወስናለን፤ ይህን ማድረግ ካልቻልን የኢትዮጵያ ችግር በአንድ ፓርቲ ወይም በሁለት ፓርቲ የሚወገድ እንዳልሆነ ግልጽ ነው፡፡ በዚህ ለወደፊት የሚደረግ ነገር ይኖር እንደሆን እንጅ ባለፈው ጉዳይ እኛበእሥር ቤት ስለነበርን በጉዳዩ አልገባንበትም፤ ወይም ምንም ሪፖርት አልደረሰንም፡፡

ሐዋርያ፡- የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ህብረት ከተመሠረተ በሁዋላ፥ በእርስዎት ይመራ የነበረው የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ህብረቱን ጥሎ በመውጣቱ በህብረት ትግሉ ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡ ይህን በተመለከተ የሚሉት ካለ ለአንባቢዎቻችን ቢገልጹልን?

ኢንጅ. ሃይሉ፡- ይህ ጉዳይ እኔን እንደሚገባኝ በሁለቱ ፓርቲዎች መካከል ከፍተኛ ቅሬታ ነበር፡፡ ይሄ ዛሬ ተቀርፎ ተቀርፎ ወደ ሌላ መልክ እየሄደ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ወቅታዊ ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም አላማችን እኛ ወደፊት የፓርቲዎች ድንበር እንዲፈርስ ነው የምፈልገው፡፡ ድንበር ሲፈር አንድነት መጣ፥ ተጠናከረ ማለት ነው፡፡ ከዚያ በሁዋላ ነጻንት ከመጣ በሁዋላ እያንዳንዱ ፓርቲ በፈለገው መንገድ ሕዝብ ሊያደራጅና በሕዝብ ፊት ሊቀርብ ይችላል፡፡ አሁን ግን የምንነታረክበት፥ የምንጋፋበት፥ የምንናቆርበርት ምንም ምክንያት የለም፡፡ እንዳሁኑ እንደተገነጠሉት ሰዎች የውስጥ ጉዳይ የለንም፡፡ ጉዳያችን ሁሉ በፊት ለፊት ነው፡፡ ስለዚህ እኛወደፊት ስንሄድ አብረን ነው የምንሄደው እንጅ በተናጠል መሄዱ ለሁለቱም ድርጅቶች የሚጠቅም አይደልም፡፡ የመፈራራት ጊዜ እለፏል፤ እስከዛሬም ድረስ ይሄ መናቆሩ ለምን እንደሆን አይገባኝም፡፡ ምናልባት፥ ምናልባት ከዳር ቁጭ ብለው ነገር በሚጎነጉኑ ሰዎች ሊሆን ይችላል፡፡ ታስታውሱ እንደሆን፥ እነ ዶ/ በየነን ያኔ ህብረቱ የተመሰረተ ጊዜ ጥያቸው ወጥቻለሁ፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች አብሬያቸው ሠርቻለሁና አውቃቸውሳለሁ፡፡ ኢሕአፓዎች በደንብ አላወቋቸውም ነበር፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ አብሬያቸው ሠርቻለሁ፡፡ ከነሱ ጋር የተሠራ
ሥራ ለወያኔ ሂዶ እንደሚሰጥ እናውቃለን፡፡ ስለዚህ ከነኝህ ጋር ህብረት ሠርቶ መሄድ ምን ለመሆን ነው? ምክንያቱም ከዚህ በፊት አይቻቸዋለሁና ነው፡፡ አሁንም ቢሆን እነዚህ ሰዎች ብቅ ብለው መጥተው እንሥራ ቢሉ አብሬ የምጓዝበት መንገድ የለም፡፡ ምክንያቱም አንድ ሰው ሥራ እሠራለሁ ሲል አፍራሽ ጎን ይዞ ሥራ አይሠራም፡፡ እና ያ በዚያ ጊዜ የነበረ ሁንታ ዛሬ ከምንነጋገረው በጣም የተለየ ነው፡፡

ሐዋርያ፡- በአሁኑ ወቅት በቅንጅትና በሌሎች የእንድነት ሃይሎች፥ ለምሳሌ ኢሕአፓ፥ ውስጥ ያለው ድርጅታዊ ችግር በመሠረቱሮን በአካሄዱ ተመሳሳይ የሆነ ጎጂ ባህርይ አለው የሚል የሕዝብ ግምገማና አስተያየት አለ፡፡ እንደርስዎ አመለካከት የችግሩ ምንጭና ለሀገራችን በእነዚህ የውስጥ እንቅስቃሴዎች አመካይነት እየተደገሰላት ያለው እጣ ፋንታ ምን ይመስልዎታል?

ኢንጅ. ሃይሉ፡- እንደዚህ ያለ ነገር ፖለቲካ ውስጥ ገብቶ መጠበቅ ያለብን ነው፡፡ ምክንያቱም እነሱ ሕዝብ ትግል ውስጥ ገብተው ትግሉ ወደፊት እንዳይቀጥል ለማድረግ ነው፡፡ በመደለልም ሆነ በሌላ ምክንያት ሰውን ለማሸሽና በሌላ ምክንያት ድሮም አለ ወደፊትም ይኖራል፡፡

የኢሕአፓን ውስጡን አላውቅም፥ የእኛ ግን ፓርቲው እንዳለ ነው ያለው፡፡ ግለሰቦች ብቻ ናቸው የወጡት፡፡ የአዲስ አበባን ጥቂት ክፍል ምናልባት ሊያሳምኑ ችለው ይሆናል፡፡ ሌላው ግን በመላው ኢትዮጵያ ያለው ከኩሩ ከእኛው ጋር ነው ያለው፡፡ ስለዚህ ቢደግሙትም ቢደጋግሙትም በግለሰብ ደረጃ ይወጣሉ እንጅ ፓርቲው አይከፈልም፡፡ ፓርቲው ተከፈለ የሚባለው በጣም ብዙወይም ግማሽ ያህል ሲወጣ ነው፡፡ የኢሕአፓ ደግሞ የበለጠ ቀላል ነው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው በሌላ መንገድ ነው፡፡ በውጭ ያለው ግን እርስ በርሱ ተነጋግሮ የማይመለሱትን እያገለለ አባሎቹን አጠናክሮ መሄድ እንጅ የሚያስቸግር ነገር አይመስለኝም፡፡ እኛ ግን ውጭ ያለውን በጥቂቱ አጠነዋል፡፡ ያንን ለመገንባት ትንሽ ጊዜ እንደሚፈጅብን ይገባኛል፡፡ ይህ ማለት ፖለቲካ ፓርቲ ፈረሰ ማለት ሳይሆን ለትግሉ የሚሆን በሃብት በገንዘብ ተዳከመ ማለት ነው፡፡

አቅማችን ወደ ሀገራችን የበለጠ ማተኮር አለበት ማለት ነው፤ መቀጠል ከፈለግን፡፡ እዚህ አሁን በጉብኝት ላይ እንዳየሁት ከሆነ፥ ሕዝቡ እውነቱን እያወቀ እየተመለሰ ነው፡፡ እናም እውነቱን እያወቀ ከመጣ ችግር የለንም፡፡ ለምን ወጠ ተመለሰ የሚል ችግር የለብንም፡፡ ምክንያቱም የፓርቲው ዋና አካል ኢትዮጵያ ውስጥ በመሆኑ እዚህ ያለውን ሁኔታ ተጨማሪ አድርገን ነው የምናየው፡፡ በኢሕአፓ ደግሞ እጃቸው ላይ ነው ያለው መፍትሄው፡፡ ማስተካከል የሚችሉ ይመስለኛል፡፡

ሐዋርያ፡- ዛሬም እንደሁልጊዜው አንገብጋቢው ነገር የአንድነት ሃይሉ መተባበር ጥያቄ ነው፡፡ ድርጅትዎ ቅንጅት ከሌሎች የአንድነት ሃይሎች ጋር ያደረጋቸው መቀራረቦች ወይም ጅምሮች ካሉ ለጋዜጣችን ታዳሚዎች ቢግልጹልን?

ኢንጅ. ሃይሉ፡- ጅማሮዎች አሉ፤ አሁን መናገር አልክፈልግም። ምክንያተቋም እንደ ከዚህ በፊቱ ተቻኩለን ውህደት አንፈጥርም። እያጠናን፥ እየፈተንን ማንነትን አውቀን የምናደርገው ነገር ስለሆነ አስቀድሜ ለሕዝብ የምናገረው ነገር አይደለም።

ሐዋርያ፡- ውያኔ/ኢህአዴግ በ2010 ዓ.ም ሌላ ምርጫ ለማድረግ እየተደገሰ ነው። ለዚህ ደግሞ እንዲረዳው አዳማቂና አጭእዋች ሊሻሆኑ የሚችሉ ክፍሎች በራሱም ሆነ በአንዳንድ የሀገሩትን አንድነትና ደህንትነ በማይሹ ሃይሎች በመደገፍ ተጠቃቅሰው ለመሰባሰብ ጥረት ጀምረዋል የሚል ትኩረት አለ። ድርጅትዎና ሌሎች የአንድነት ሃይሎች ይህን አዝማሚያ እንዴት ይከታተሉታል?

ኢንጅ. ሃይሉ፡- ከሕዝብ ምንም ከሚያደርገው በላይ ማድረግና መጠበቅ የለብንም። የእኛ ሕዝብ ያ ሁሉ ችግርና መከራ ደርሶበት ከእኛ ጋር  ተመልሶ መሥራቱን እኔ ትልቅ ታእምር አድርጌ ነው የማየው። አሁንበየቀኑ ሪፖርት ይደርሰኛል። ሕዝቡ ከእኛ ጋር እየሄደ ነው። መታገል ይፈልጋል። አንዳንዶቹ ሕዝቡ የተፈጠረውን ችግር ሲሰማ እንደ ጅብ ጎሬው እንደሚገባ፥ በየቤቱ ገብቶ ገብቶ ይደበቃል የሚሉ እንደነበር ይታወቃል። ግን አላደረገውምን። ይሄው ወጥቶ ትግሉን እያካሄደ ነው። ገጠሩን አሁን እንደገና አዋቅረነዋል። ትንሽ ችግር ያለው አዲስ አበባ ነው። እሱን ደግሞ ቀስ በቀስ እናስተካክለዋለን የሚል እምነት ስላለ ከሕዝብ በኩል ያለው ሁኔታ ችግር አይኖረውም። ችግር የሚኖረው ምርጫ በሚቃረብበት ጊዜ እኛ አንቀርብም ስንል ላይገባው ይችላል። እስከዚያ ድረስም እናስተምረዋለን፤ ምርጭእችን መቸ እንደሆን እናሳየዋለን የሚል እምነት ስላለን ችግሩ ገና ሳይጀምር ይመጣል ብዬ መገመቱ ጥሩ ነገር አይመስለኝም።

ሐዋርያ፡-  በአሁኑ ወቅት በውጭ ሀገሮች ያሉት የቅንጅት አባላትና ደጋፊዎች በምን ሁኔታ ላይ ይገኛሉ?

ኢንጅ. ሃይሉ፡- ከፍተኛ ውዥንብር ወይም ግራ መጋባት አለ። አንዳንዱ በልቡ ለማድረግ የፈለገውን የፈራበት ሁኔታ አያለሁ፥ እዚህ አሜሪካ አገር ሆኖ። ይሄ በአጭር ጊዜ ውስጥ ይፈታል ብዬ አልገምትም። ሰበብ ፈልጎ ገለል ያለም አለ። ስለዚህ እዚህ ያለን ሃይል ግንባታ ቀላል አይደለም፥ ጊዜ ይፈጃል። በጣም ብዙ ጠንካራ ሰዎች ያስፈልጉናል። በዚያ መንገድ በሃይል ከተሠራ ነው እንጅ ያዝ ለቀቅ በማድረግ የቅንጅት ድጋፍ ጠንካራ ሆኖ ሊቀጥል የሚችል አይመስለኝም። እኔ ተስፈኛ ስለሆንኩ፥ ከአንድ ዓመት በሁዋላ ብትጠይቀኝ  በደምብ ልነግርህ እችላለሁ ።

ሐዋርያ፡- የዓልም አቅፉን ሁኔታና  ከመንግሥታቱ ጋር ያለውን ግንኙነት እንደት ይረዱታል?

ኢንጅ. ሃይሉ፡- እንዲህ ነው የዓለም አቀፉ ሁኔታ፤ ስለዚህም ነው ትግሉ ተጠናክሮ መሄድ አለበት የምንለው። ምክንያቱም ብዙ ጊዜ ስህተት አድርገናል። ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እኛን ይደግፋሉ፥ ለዴሞክራሲ ቆመዋል የሚባል ብዙ ወሬ አለ። ይሄንን በአሁኑ የትግል ሂደት ትክክል እንዳልሆነ ተረድተናል። ስለዚህ እኛ በራሳችን ሰዎች፥ በኢትዮጵያና ውጭ ባሉ ወገኖቻችን መመካት እንጅ ሌሎች ዓለም አቀፍ ድርጅቶች መጥተው ይረዱናል ብሎ መገመቱ ከንቱ ነው። አንዳንዶቹ ቢበዛ ትንሽ ይጮሃሉ እንጅ ከዚያ በላይ ምንም ነገር የለም። እኛ ደግሞ የራሳችንን ሥራ ከሠራን፥ ጠንካራ ሆነን ከቀረብን በሁዋሮል፥ ሌሎች ቢረዱን ባይረዱን የሚቀርብን ነገር የለም። ጥንካሬ ብቻ ነው የሚያስፈልገው።

ሕዋርያ- በጣም እናመሰግናለን!

ኢንጅ. ሃይሉ- እኔም አመሰግናለሁ።